በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት
ለፌደራል የተቀናጀ የመሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ
አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- የኤጀንሲውን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርትን ይመለከታል፤

በርዕሱ የተጠቀሰውን ኤጀንሲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 24 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 5 ገጽ አባሪ በድምሩ 29 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል። በመሆኑም በገጽ 30 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ
የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት

የፌደራል የተቀናጀ የመሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት

የፌደራል የተቀናጀ የመሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የፌደራል የተቀናጀ ልማት ማስተባበሪያ ኤጀንሲ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል።

ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን የኤጀንሲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው።

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ኦዲታችን የሚያካትተው፡ -

- ✓ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- ✓ የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- ✓ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል።

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል።

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም።

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን።

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የፌደራል የተቀናጀ የመሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

የፌደራል የተቀናጀ የመሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ሥራ አመራር በ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር OFAGF-02.6/3/2 በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት ኤጀንሲው ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር መልኤ/562/10 በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል። በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. የወጪ ሂሳብ

1.1 በግዥ መመሪያው መሰረት ያልተፈጸመ የቢሮ ኪራይ ጨረታ ግምገማ ፤

1.1.1 ግኝት

የፌዴራል የተቀናጀ መሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ነሐሴ 3/2008 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባወጣው የቢሮ ኪራይ ማስታወቂያ መሰረት ሶስት ተወዳዳሪዎች ለቴክኒካል ግምገማ እንዲቀርቡ የተደረገ ሲሆን፣ በተዘጋጀው የቴክኒካል ግምገማ ከ80% በላይ ያመጡ ተወዳዳሪዎች ብቻ ለፋይናንሻል ግምገማ እንደሚያልፉ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት አቶ ሰለሞን ሹፌር የተባሉት ተጫራች የቴክኒካል ግምገማውን በብቸኝነት በማሸነፋቸው በአቀረቡት የመጫረቻ ዋጋ መሰረት በየዓመቱ በካሬ ሜትር ዋጋው ላይ 5% ጭማሪ እየተደረገ ለአምስት ዓመት የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ባቀረቡት ዋጋ ብር 43,921,920.00 መሰረት ከኤጀንሲው ጋር ጳጉሜ 3/2008 ዓ.ም ውል ተፈርሟል። ከመስከረም 2009 ዓም አስከ ሰኔ 2009 ዓ.ም ድረስ ያለው የአሥር ወራት የቤት ኪራይ ክፍያም የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ብር 6,624,000.00 ተፈጽሟል፡ ፡ ሆኖም የጨረታው ሂደት አግባብነት ሲጣራ፡-

1. በግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 8(ለ) መሰረት እንዲሁም በግዥ መመሪያው ክፍል 2 አንቀጽ 5(10) መሰረት የመሥሪያ ቤቱ

ኃላፊ ውስብስብ ለሆኑ እና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚፈልጉ ግዥዎች ጊዜያዊ ገምጋሚ ኮሚቴ ማቋቋም እንደሚችል በተደነገገው መሰረት የቢሮ ኪራይ ጨረታውን ሂደት የሚገመግም 3 አባላት ያሉት ኮሚቴ ተቋቁሞ ግምገማውን ለማከናወኑ እና የኮሚቴው አባላት በቴኪኒካልና በፋይናንሻል ውጤቱ ላይ የሚስማሙ ለመሆኑ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ነሐሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም ለኮሚቴው አባላት በጻፉት ደብዳቤ ላይ በፊርማቸው አረጋግጠዋል። በግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 8(ለ) መሰረት እንዲሁም በግዥ መመሪያው ክፍል 2 አንቀጽ 5(4) የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ እንዲቋቋም ባለመደረጉ በግዥ ገምጋሚ ኮሜቴው የተከናወነውን ግምገማ የኤጀንሲው ኃላፊ ያጸደቁት ለመሆኑ ከቀረበው ደብዳቤ ለመረዳት ተችሏል።

2. ሰኔ 2002 ዓም በወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል አራት አንቀጽ 16.5 መሰረት በኤጀንሲው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ተዘጋጅቶ ተጫራቾች የቴክኒካል መስፈርቱን ሞልተው አቅርበዋል። ሆኖም የቴክኒካል ግምገማው ሲደረግ ሁለቱ ተጫራቾች ዶ/ር ገ/እግዚሐብሄር አለበል ህንጻ እና ዘሪሁን ደስታ ኢንተርፕራይዝ በተራ ቁጥር 1 እና 2 እንዲሁም በተራ ቁጥር 3 ከተመለከቱት ዝርዝር የመገምገሚያ መስፈርቶች ውስጥ የመጨረሻውን የመገምገሚያ ነጥብ ሳይጨምር አሸናፊ ከሆኑት ተጫራች የተሻለና ተቀራራቢ የሆነ ውጤት ያመጡ ቢሆንም በተራ ቁጥር 3 ከተመለከቱት ዝርዝር መገምገሚያ መስፈርቶች ውስጥ ቢያንስ 20 የኤጀንሲውን መኪኖች ማስተናገድ የሚችል ፓርኪንግ ያለው ለሚለው ለመጨረሻው መገምገሚያ መስፈርት ከተቀመጠው 15% አሸናፊው ተጫራች 15% ሲሰጣቸው ለሁለቱ በቴክኒካል መስፈርቱ ለወደቁት ተጫራቾች ግን 0% ሊሰጥ ችሏል። ነገር ግን ሁለቱም ተጫራቾች ሞልተው ባቀረቡት የቴክኒካል መስፈርት ላይ ይህን እንደሚያሟሉ የገለጹ ከመሆኑም በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት

በአደረግነው ማጣራት ሁለቱም ተጫራቾች በቂ የመኪና ማቆሚያ ቦታ እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል። ነገር ግን ለፋይናንሻል ግምገማው እንዳያልፉ የተደረጉ መሆኑ፤

3. በግዥ መመሪያው ክፍል 4 አንቀጽ 16.18.3 መሰረት ጨረታው በሁለት ኤንቨሎፖች እንዲቀርብ የተጠየቀ ሲሆን፣ የቴክኒክ ግምገማ ተደርጎ የተገኘው ውጤት ሥልጣን በተሰጠው አካል ከጸደቀ በኋላ ወጤቱ በጨረታው ለተሳተፉ ተጫራቾች በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ በጽሁፍ መገለጽ እንዳለበት እና በተለይም የቴክኒክ ግምገማውን ላላለፉት ተጫራቾች የሚጻፈው ደብዳቤ በጨረታው የተሸነፉበትን ምክንያት የሚገልጽ መሆን እንዳለበት ተመልክቷል። ሆኖም የቴክኒክ ግምገማውን ላላለፉት ተጫራቾች የተጻፈ ደብዳቤ ካለ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤

ታውቋል።

1.1.2 <u>ሥጋት</u>

የግዥ አዋጁን እና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን ያለመፈጸም፡ -

- ☞ የጨረታ ሂደቱን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።
- ☞ ግልጽ አሰራር እንዳይኖር እና የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ☞ ለጥቅም ትስስር መንገድ ሊከፍት ይችላል።
- ☞ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

1.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት በግዥ ክፍል ወይም በመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ በተቋቋመ ጊዚያዊ የግዥ ገምጋሚ ኮሚቴ ተገምግሞ የቀረበው የጨረታ ሂደት በመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ በሚቋቋም የጨረታ አጽዳቂ ኮሚቴ በቃለጉባኤ ተደግፎ መጽደቅ ነበረበት። ስለሆነም የግዥ አዋጁና መመሪያው ተከትሎ ያልተፈጸመ የጨረታ ሂደት ተዓማኒነት

የሌለውና ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለሆነ ኤጀንሲው የግዥ አዋጁና በመመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን መፈጸም እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በግዥ መመሪያው መሰረት ያልተፈፀመ የቢሮ ኪራይ ጨረታ ግምገማ የተመለከተ በመንግስት የወጣውን የግዥ አዋጅና መመሪያ በአግባቡና በስርዓቱ ተግባራዊ አለመደረጉ የተረዳን ስለሆነ ይህንን ስህተት ዳግም እንዳይፈፀም አስፈላጊው ጥንቃቄና የተጠያቂነት ስርዓት የሚቀመጥ ይሆናል።

1.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ኤጀንሲው የተሰጠውን ኃላፊነት መወጣት የሚችለው በቅድሚያ በመንግሥት የወጣውን የግዥ አዋጅና መመሪያ በአግባቡና በሥርዓቱ ተግባራዊ ሲያደርግ ነው።

1.2 የቤት ኪራይ የጨረታ ግዥ ቴክኒካል ግምገማ በአግባቡ ባለመከናወኑ ምክንያት አለአግባብ ከመንግሥት ካዝና ገንዘብ ወጪ ስለመደረጉ፤

1.2.1 ግኝት

የፌዴራል የተቀናጀ መሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ነሐሴ 3/2008 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የቢሮ ኪራይ ማስታወቂያ ያወጣ ሲሆን በማስታወቂያ ከተገለጹት ውስጥ ተጫራቾች በዋንኛነት ሊያሟሏቸው ከሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ "ህንጻው ጥራቱን ጠብቆ የተሰራና ያለቀለት፣ የፌዴራል የመሰረተ ልማት መሥሪያ ቤቶች (መብራት ኃይል፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ ቴሌ) በአካባቢ የሚገኝ፤ በቂ የሆኑ የቢሮ አገልግሎቶች ማለትም እንደ መጸዳጃ ቤት (ለወንድና ለሴት ለየብቻ)፣ ውሃ፣ መብራት፣ የስልክና የኢንተርኔት አገልግሎት እና ሌሎችም ያለው መሆን እንዳለበት" ተመልክቷል፡፡

ሆኖም፡ -

1. ከላይ በተራ ቁጥር 1 ከቀረበው ግኝት ለመረዳት እንደተቻለው ጨረታውን ያሸነፋት ግለሰብ በቴክኒካል ግምገማ ብቸኛ አሸናፊ ከሆኑ በኋላ ኤጀንሲው ነሐሴ 1 ቀን 2008 ዓ.ም (እ.ኤ.አ መስከረም 6 ቀን 2016) በደብዳቤ ቁጥር FIDCA/025/16 ለግለሰቡ በጻፈው ደብዳቤ የመስክ ጉብኝት በተደረገበት ወቅት የታዩትን ክፍተቶች በ30 ቀናት ያለምንም ዋጋ ለውጥ ድርጅቱ ራሱ እንዲያስተካከል ካልሆነ ግን ኤጀንሲው ወደ ውል ስምምነት እንደማይገባ የገለጸ ቢሆንም አከራይ ድርጅቱ ምንም አይነት ማስተካከያ ሳያደርግ ኤጀንሲው ነሐሴ 3 ቀን 2008 ዓ.ም (እ.ኤ.አ መስከረም 8 ቀን 2016) የውል ስምምነት ተፈራርሞ የአሥር ወራት የቤት ኪራይ ቅድሚያ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

2. ኤጀንሲው የተከራየው ህንጻ የተፈለገውን የኤሌክትሪክ ኃይል ያላሟላ በመሆኑና የኢንተርኔት መስመር ዝርጋታው ያልተጠናቀቀ በመሆኑ የኤሌክትሪክ ኃይል ለመጨመር በሚል ብር 615,221.29 በህንጻ አከራዩ በአቶ ሰለሞን ሹፌር ሃብቴ ስም ለመብራት ኃይል ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

3. ኤጀንሲው የኔት ወርክ ዝርጋታውን ለፈጸመው ድርጅት የሚከፈል በሚል ወደ አከራዩ አካውንት ብር 138,000.00 በማዘዋወር ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

በአጠቃላይ ኤጀንሲው በጨረታ ማስታወቂያ መሰረት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች ሳይሟሉ የኪራይ ውል በመፈጸሙ ለተጨማሪ ሥራዎች በድምሩ ብር 753,221.29 አላግባብ ከመንግሥት ካዝና ወጪ እንዲሆን ያደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ገንዘቡ ከአከራይ ድርጅቱ እንዲተካ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

1.2.2 ሥጋት

ኤጀንሲው ባወጣው የቤት ኪራይ የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች ሳይሟሉ ግለሰቡን አሸናፊ እንዲሆኑ በመደረጉ፡-

- ☞ የጨረታ ሂደቱን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።
- ☞ ግልጽ አሰራር እንዳይኖር እና የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ☞ ለጥቅም ትስስር መንገድ ሊከፍት ይችላል።
- ☞ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

1.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ኤጀንሲው ባወጣው የቤት ኪራይ የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች ሳይሟሉ ግለሰቡ አሸናፊ እንዲሆኑ በመደረጉ ምክንያት የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በላይ የጨረታ ሂደቱ ተዓማኒነት የሌለው መሆኑን በግልጽ ያመለክታል። ስለሆነም በጨረታ ግምገማ ሂደቱ ላይ በተሳተፉት፣ ባጸደቁት እና አለአግባብ የመንግሥት ገንዘብ ወጪ እንዲሆን በፈቀዱት ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም አለአግባብ ወጪ የተደረገው የመንግሥት ገንዘብ በአስቸኳይ ተመላሽ እንዲሆን እናሳስባለን።

1.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

የቤት ኪራይ የጨረታ ግዥ ቴክኒካል ግምገማ በአግባቡ ባለመከናወኑ ምክንያት አለአግባብ ከመንግሥት ካዝና ገንዘብ ወጪ ለመደረጉ የቀረበውን የማሻሻያ ሃሳብ የምንቀበለው ሲሆን ለብር 753,221.29 (ሰባት መቶ ሃምሳ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ አንድ ብር ከ29/100) ከ2010 በጀት ዓመት የቤት ኪራይ ተቆርጦ ለመንግሥት ካዝና ገቢ እንደሚደረግ ለአከራዩ ደብዳቤ የተጻፈ ስለሆነ በቀረበው ማሻሻያ ሃሣብ መሰረት እርምጃ የምንወስድ ይሆናል።

1.2.5 የኦዲተሩ አስተያየት

በወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት ሳይፈጸም ገንዘብ ከመንግሥት ካዝና ወጪ እንዲሆን መደረጉ አግባብ አይደለም። ስለሆነም በማሻሻያ ሃሳቡ ላይ በተገለጸው መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል።

1.3 ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ በውስን ጨረታ የተፈጸመ ግዥ፤

1.3.1 ግኝት

ሰኔ 2002 በወጣው የግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 49 እና የግዥ አፈጻጸም መመሪያውን እንደገና ለማሻሻል ታህሳስ 2008 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሰረት ግዥን በውስን ጨረታ መፈጸም የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ለመሆኑ ተመልክቷል። ይኸውም:-

1. ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
2. የግዥው መጠን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን፣ ወይም
3. ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያው የሚገለጽ ሆኖ በተደጋጋሚ ጨረታ ወጥቶ ተወዳዳሪ ያልተገኘ ሲሆን፣

ለመሆኑ ተመልክቷል።

ስለሆነም በአዋጁ መሰረት በውስን ጨረታ ግዥ ለመፈጸም መሟላት ያለበት በአዋጅ አንቀጽ 49 (1) እና (2) የተመለከቱት ሲሟሉ ብቻ መሆን ይኖርበታል።

በግዥ አዋጁ አንቀጽ 49(3) በተገለጸው መሰረት ደግሞ ግዥን በውስን ጨረታ ለመፈጸም በቅድሚያ ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 23(4) መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች በቅደም ተከተል መሟላት ይኖርባቸዋል። ይኸውም:-

1. ግዥውን ለመፈጸም የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ ለሁለት ጊዚያት ወጥቶ ምንም ተጫራች ያልቀረበ ወይም በድጋሚ ቢወጣ የቀረቡት ተጫራቾች በመሥሪያ ቤቱ የተዘጋጀውን የቴክኒክ ፍላጎት ያላሟሉ መሆኑን፣

2. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የጨረታ ጥሪውን፣ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ መጠን እና አይነት እንዲሁም ሌላ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለመሳተፍ እንዳይችሉ የሚገድቡ ሁኔታዎች በአሰራሩ ወይም በጨረታ ማስታወቂያ ሰነዱ ውስጥ አለመኖራቸውን፣

3. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በመስኩ የተሰማሩት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ ግዥው ቢጋበዙ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲያምን፣

4. እስከታቻለ ድረስ በመስኩ የተሰማሩት አቅራቢዎች በግልጽ ጨረታ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ያልሆኑበትን ምክንያት በማጣራት ምክንያታቸው ሕጋዊ እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቱን ጥቅም ለመጉዳት ያለመሆኑ፣ እንዲሁም

5. በዉስን ጨረታ የግዥ ዘዴ መጠቀም የሚቻለዉ የሚገዛዉ ዕቃ ጠቅላላ ዋጋ ከብር 1,500,000.00 የማይበልጥ ከሆነና ቢያንስ አምስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለመጋበዛቸው፣

በቅደም ተከተል መሟላታቸው መረጋገጥ እንዳለባቸው ተመልክቷል። በተጨማሪ በግዥ መመሪያው አንቀጽ 31 መሰረት መደበኛ ያልሆኑ የግዢ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ በመመሪያው ላይ የተዘረዘሩትን የግዢ አፈጻጸም ሥርዓቶች መጠበቅ ካልተቻለ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዥ ለመፈጸም ካስፈለገ በቅድሚያ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት የግዥ ኤጀንሲን ማስፈቀድ እንደሚያስፈልግ ተገልጿል። ሆኖም ኤጀንሲው ግልጽ ጨረታ ሳያወጣና በውስን ጨረታ ግዥን ለመፈጸም የተቀመጡት መስፈርቶች ሳይሟሉ እንዲሁም የግዥ ኤጀንሲን ሳያስፈቅድ በብር

2,320,734.72 የፈርኒቸር ዕቃዎች ግዢ በውስን ጨረታ የፈጸመ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

1.3.2 ሥጋት

- ☞ በግዢ አፈጻጻም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል፡ ፡
- ☞ የመንግሥት ግዢ አፈጻጸምን ቀልጣፈና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ እንዳይቻልና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል ያደርጋል፡ ፡
- ☞ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡ ፡
- ☞ የግዥ አዋጁን እና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡ ፡

1.3.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ኤጀንሲው ግዥዎች በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡ ፡

1.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ በውስን ጨረታ ግዥው መፈጸሙ ስህተት መሆኑን ተቀብለን ከዚህ ስህተት በመነሳት ግዥዎች በግዥ አዋጅና መመሪያው መሰረት እንዲፈፀሙ ተገቢውን ከትትልና ቁጥጥር የምናደርግ ይሆናል።

1.3.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ኤጀንሲው ግዥውን በውስን ጨረታ ማካሄድ እንዲችል የግዥ ኤጀንሲን ይሁንታ በጠየቀበት ወቅት አዋጁና መመሪያው በሚፈቅደው አግባብ ግዥውን መፈጸም እንደሚችል የተገለጸለት ቢሆንም በመመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ ግዥውን መፈጸሙ ተገቢ አይደለም። የግዥ አዋጁንና

መመሪያውን ተከትሎ ግዥ ያለመፈጸም የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በላይ አሰራሩ ተጠያቂነትን ያስከትላል። የግዥ አፈጻጸም መመሪያውን እንደገና ለማሻሻል ታህሳስ 2008 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሰረት እስከ ብር 1,500,000.00 የሚፈጸሙ የዕቃ ግዥዎችን በውስን ጨረታ መፈጸም የሚቻለው በቅድሚያ ከላይ በግኝቱ ላይ የተገለጹት መስፈርቶች ከተሟሉ መሆን ይኖርበታል።

በመሆኑም ለወደፊቱ ኤጀንሲው ግዥዎችን የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትሎ መፈጸም እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

1.4 ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ በፕሮፎርማ የተፈጸመ ግዥ፤

1.4.1 ግኝት

ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል በወጣው መመሪያ መሰረት ከብር 200,000.00 በላይ ለሚፈጸሙ የዕቃ ግዥዎች ግልጽ ጨረታ መውጣቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኤጀንሲው በብር **503,073.92** የፈጸማቸውን የፈርኒቸር እቃዎች ግዥ በግልጽ ጨረታ መፈጸም ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የፈጸመ መሆኑ ታውቋል።

(ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)

1.4.2 ሥጋት

- ☞ በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችልለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል።
- ☞ የመንግሥት ግዢ አፈጻጸምን ቀልጣፈና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ እንዳይቻልና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል ያደርጋል።
- ☞ ግልጽ አሰራር እንዳይኖር እና የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

☞ የግዥ አዋጁን እና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

1.4.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኤጀንሲው ግዥዎች በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

1.4.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገባው ከተፈቀደው ወሰን በላይ በፕሮፎርማ ግዥ መፈጸሙ ስህተት መሆኑን ተቀብለን ከዚህ ስህተት በመነሳት ግዥዎች በግዥ አዋጅና መመሪያው መሰረት እንዲፈፀሙ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የምናደርግ ይሆናል።

1.4.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትሎ ግዥ ያለመፈጸም የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በላይ አሰራሩ ተጠያቂነትን ያስከትላል። ስለሆነም በግዥ መመሪያው አንቀጽ 31 መሰረት መደበኛ ያልሆኑ የግዢ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመመሪያው ላይ የተዘረዘሩትን የግዢ አፈጻጸም ሥርዓቶች ሊጠብቁ ካልቻሉ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዢ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ለግዥ ኤጀንሲ አቅርበው ሲፈቀድላቸው ብቻ መሆን እንዳለበት ተመልክቷል። በመሆኑም ኤጀንሲው በቅድሚያ የግዥ ኤጀንሲን ማስፈቀድ ነበረበት።

1.5 <u>የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈፀሙ ግዢዎች</u>፤

1.5.1 <u>ግኝት</u>

ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል በወጣውና መመሪያ መሰረት እስከ ብር 200,000.00 ድረስ ለሚፈጸሙ የዕቃ ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኤጀንሲው በብር

100,100.33 ለፈጸማቸው የዕቃ ግዥዎች በመመሪያው መሰረት እስከተቻለ ድረስ ከሶስት ድርጅቶች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰብ ሲገባው የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ ግዥውን የፈጸመ መሆኑ ታዉቋል።

(ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል)

1.5.2 ሥጋት

- ☞ በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል።
- ☞ የመንግሥት ግዢ አፈጻጸምን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ እንዳይቻልና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል ያደርጋል።
- ☞ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- ☞ የግዥ አዋጁን እና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

1.5.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ኤጀንሲው የሚፈጽማቸው ግዥዎች በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

1.5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈፀመ ግዥ በተመለከተ ከሶስት ድርጅቶች ፕርፎርማ ሳይሰበሰብ ግዥ መፈፀሙ ስህተት መሆኑን ተቀብለን ከዚህ ስህተት በመነሳት ግዥዎች በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት እንዲፈፀሙ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የምናደርግ ይሆናል።

1.5.5 <u>*የኦዲተሩ አስተያየት*</u>

የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትሎ ግዥ ያለመፈጸም የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በላይ አሰራሩ ተጠያቂነትን ያስከትላል።

በግዥ መመሪያው አንቀጽ 31 *መሰረት መደበኛ ያልሆኑ የግዢ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመመሪያው ላይ የተዘረዘሩትን የግዢ አፈጸጸም ሥርዓቶች ሊጠብቁ ካልቻሉ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዢ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ* 16 *ንዑስ አንቀጽ* 5 *መሰረት ለግዥ ኤጀንሲ አቅርበው ሲፈቀድላቸው ብቻ መሆን እንዳለበት ተመልክቷል፡ ፡ ስለሆነም ኤጀንሲው በቅድሚያ የግዥ ኤጀንሲን ማስፈቀድ ነበረበት።*

1.6 <u>*የግዥ ዕቅድ ያልተዘጋጀ ስለመሆኑ*</u>፤

1.6.1 <u>*ግኝት*</u>

ሰኔ 2002 *ዓ.ም በወጣዉ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል* 3 *አንቀፅ* 8 *ቁጥር* 1 *መሰረት ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤትና በስሩ የተደራጁ አካላት የታቀዱ የስራ ፕሮግራሞቻቸዉን ተግባራዊ ለማድረግ ይችሉ ዘንድ የሚያስፈልጋቸዉን ግዥ በወቅቱ ለመፈጸም የሚያስችል በመርሃ ግብር የተደገፈ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት እንዳለባቸውና ዕቅዱ ለግዢ ኤጀንሲ መላክ እንዳለበት ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በ*2009 *በጀት ዓመት የግዥ እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ ታውቋል።*

1.6.2 <u>*ሥጋት*</u>

የግዥ ዕቅድ ካልተዘጋጀ፡-

- ☞ *ግዥውን በዕቅድ መምራት አይቻልም።*
- ☞ *የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ ሊወጣ ይችላል።*

1.6.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በግዢ አፈጻጸም መመሪያው መሰረት ግዥ ከመፈጸሙ በፊት የግዥ ዕቅድ ተዘጋጅቶና በኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ ጸድቆ ለግዥ ኤጀንሲ መላክ ይኖርበታል፡፡ ግዥም ሲፈጸም በዕቅዱ መሰረት መከናወን ይኖርበታል፡፡

1.6.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የግዥ አቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑ ተገልጾ የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሣብ ተቀብለን የ2010 በጀት ዓመት የግዥ እቅድ አዘጋጅተን ለግዥ ኤጀንሲ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

2. <u>ንብረት</u>

2.1 <u>በንብረት አስተዳደር ላይ የታዩ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ክፍተቶች</u>፤

2.1.1 <u>ግኝት</u>

የኤጀንሲው የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ✓ በኤጀንሲው ያሉ ቋሚ ንብረቶች ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎችን ለእያንዳንዱ ንብረት የታሪክ ማህደር በመክፈት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባዘጋጀው ቅጽ መሠረት ወይም የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ሥርዓት በመጠቀም ያልተመዘገበ መሆኑ፤
- ✓ የንብረት ተጠቃሚ ሠራተኞች የንብረት ምዝገባ ካርድ (User Card) ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- ✓ በኤጀንሲው ጥቅም ላይ ለዋሉ ቋሚ ንብረቶች በሙሉ የንብረት መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤

- ✓ በንብረት ወጪ ደረሰኝ ዲስክ ቶፕና ላፕቶፖች ወጪ ሲሆኑ የሞዴልና ሴሪያል ቁጥራቸው እንዲሁም ዋጋቸው ያልተገለጸ መሆኑ፤
- ✓ በዕቃ ግምጃ ቤት ለሚገኙ ስቶኮች ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤
- ✓ የሞባይል ካርድ ግዢ ተፈጽሞ በንብረት ገቢ ደረሰኝ (በሞዴል 19) ገቢ ያልተደረጉ ሲሆን እንዲሁም ጥቅም ላይ ሲውሉ በንብረት ወጪ ደረሰኝ (በሞዴል 22) ወጪ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ የነዳጅ ኩፖን ወጪ ሲሆን የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
- ✓ ለመሥሪያ ቤቱ ሶስት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ በሚፈለግበት ወቅት በነዳጅ ወጪ መጠየቂያ ቅጽ ያልተጠየቀ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

2.1.2 ሥጋት

- ☞ ኤጀንሲው መንግሥት ያወጣዉን የንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ ተከትሎ የማይፈጸም ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- ☞ የመንግሥት ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ኤጀንሲው የንብረት አስተዳደሩን መንግሥት ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ማስተካከል ይኖርበታል፡፡

2.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በንብረት አስተዳደር ላይ የታዩ የውስጥ ቁጥጥር ሰርዓት ክፍተቶች በተመለከተ በኦዲት ግኝት የተዘረዘሩት ችግሮች ሙሉ በሙሉ የምንቀበላቸውና መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ወስደን በተሰጠን ማሻሻያ ሃሣብ መሰረት፡-

1. በኤጀንሲው ጥቅም ላይ ለሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር የተሰጠ መሆኑን፣

2. ስቶክ ካርድና ቢን ካርዶች ታትመው ወደ ሥራ እንዲገባ በሂደት ላይ መሆኑን፣

3. ለቋሚ ንብረት ተጠቃሚ ሰራተኞች የንብረት ምዝገባ ካርድ የተዘጋጀ መሆኑን፣

4. ዲስክ ቶኘና ላፕ ቶኘ ወጪ በሆኑበት የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ላይ ዋጋቸውና ሲሪያል ቁጥራቸው እንዲሞላ እየተደረገ የሚገኝ መሆኑን፣

5. ለፑል አገልግሎት እየተጠቀምንባቸው የሚገኙ ሶሰት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ መጠየቂያና ማዘዣ የተዘጋጀና ተግባር ላይ የዋለ መሆኑን፣

እየገለጽን በአጠቃላይ የነበሩብንን ክፍተቶች መንግሥት ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ማስተካከል እንደሚገባንና በአጭር ጊዜ እንደምናሻሽል ለማረጋገጥ እንወዳለን።

2.2 <u>የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ</u>፤

2.2.1 <u>ግኝት</u>

በኤጀንሲው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ሥምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- የተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ ዘይት እና ቅባት ፍጆታ መጠን የጥገና ወጪ የተጓዘው ኪ.ሜ መጠን የጥገና ወጪ በማን ይዞታ ስር እንደነበረ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑ፣

- ከመንግስት ተሽከርካሪዎች ምዝገባ አያያዝ ስምሪት እና አጠቃቀም ጋር በተገናኘ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚገባቸው ቅጾች ስራ ያልዋሉ መሆኑ፣
- ለመኪና ጥገና ከግምጃ ቤት ወጪ የተደረጉ መለዋወጫዎች በተሽከርካሪው ላይ በትክክል መገጠሙ አግባብነት ባለው ባለሙያ ያልተረጋገጠ መሆኑ፣
- ለበላይ ኃላፊዎች እና ለኃላፊዎች ከሚመደቡ ተሽከርካሪዎች በስተቀር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ ያልቀረበ መሆኑ፣

ታውቋል።

2.2.2 ሥጋት

በመመሪያው መሰረት ያለመፈጸም በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።

2.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

በኤጀንሲው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ሥምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ መሰረት እንዲፈጽም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡ ፡

2.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ የተገኙት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች የምንቀበላቸው ሲሆን የፑል ተሽከርካሪዎች መውጫ በመሙላት የሚሞሉት የነዳጅ፣ የዘይትና የቅባት መጠን ተመዝግቦ እንዲያዝ እየተደረገ ይገኛል። እንዲሁም በተሽከርካሪ ሥምሪት መመሪያ የተቀመጡት ቅጾች ስራ ላይ እንዲውሉ እየተደረገ ይገኛል። ሆኖም ግን ቀጣይ ችግር ሆኖ የሚቀጥለው የተሽከርካሪ መለዋወጫ እቃዎች በትክክል በተሽከርካሪው ስለመገጠሙ የሹፌር መካኒክ መደብ ጠይቀን አይፈቀድም በመባሉ ምክንያት ቀጣይ ችግር ሊሆን ይችላል።

2.2.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ኤጀንሲው የፌዴራል መንግሥት ባወጣው የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሠረት አሰራሩን እንዲስተካከል እናሳስባለን፡፡

3. በጀት

3.1 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት፤

3.1.1 ግኝት

ለኤጀንሲው ለ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደው የመደበኛ በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር 2,980,892.16 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል)

3.1.2 ሥጋት

የወጪ ሂሣብ በጀቱ በእቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የኤጀንሲው ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

3.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

የዓመቱ በጀት ስራ ላይ ለማዋል በተቻለ መጠን ጥቅም ላይ ለማዋል የተሰራ ቢሆንም የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሣብ ተቀብለን በዚሁ በጀት ዓመት በጀቱን በአግባቡና በህጉ መሰረት ለመጠቀም ጥረት ይደረጋል፡፡

(ለዝርዝር ምላሹ አባሪ 6 ተያይዟል)

3.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ኤጀንሲው በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል። በተጨማሪም ኤጀንሲው የበጀት አጠቃቀሙ ላይ ክትትል በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

4. ልዩ ልዩ

4.1 ለሰራተኞች ቅጥር የቃል እና የጽሑፍ ፈተና የተደረገበት ማስረጃ ያልቀረበ ስለመሆኑ፤

4.1.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 16/3 መሠረት የቅጥር አፈጻጸም የሚሆን የማወዳደሪያ መስፈርት የተዘጋጀ መሆኑን እና የቅጥርና የዝውውር ሂደቱን አግባብነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኤጀንሲው የመጀመሪያ ዙር የሰራተኞች ቅጥር ለመፈጸም የካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሄራልድ ጋዜጣ በወጣው ማስታወቂያ መሠረት ስለቅጥሩ ሁኔታ በተያዘው ቃለ ጉባኤ መሠረት አመልካቾች ባቀረቡት ተፈላጊ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ መሰረት በኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር እና ዋና ዳይሬክተሩ ከቀረቡት አመልካቾች መካከል ቅጥሩን ሊፈጽሙ ይችላሉ ብለው ያመኑባቸውን እጩ ተቀጣሪዎች በሰራተኞች የቅጥር ሂደት ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በጽህፈትና በቢሮ አስተዳደር የትምህርት ዘርፍ የተመረቁትን በኮምፒዩተር የጽሁፍ፣ የተግባር እና የቃል ጥያቄ ፈተና በመፈተን በቂ ውጤት በማምጣት ያለፉትን ተወዳዳሪዎች ብቻ ተቀጣሪ እንዲሆኑ መደረጉን የቅጥርና የዝውውር ከተፈጸመበት ቃለ ጉባኤ ለመገንዘብ የተቻለ ቢሆንም፡ -

- እጩ ተቀጣሪዎች በሰራተኞች የቅጥር ሂደት ላይ እንዲሳተፉ መደረጉ፤
- የጽሁፍና የቃል ፈተና ውጤታቸውን የሚሳይ ማስረጃ ለኦዲት ሊቀርብ አለመቻሉ፤ (ለዝርዝሩ አባሪ 8 ተያይዟል)
- ለቅጥርና ለዕድገት የሚሆን የማወዳደሪያ መስፈርት የተዘጋጀ ቢሆንም ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያልተላከ መሆኑ፤

ታውቋል።

4.1.2 <u>ሥጋት</u>

ለተቀጣሪዎች የቀረበው የጽሁፍና የቃል ፈተና ውጤታቸውን የሚሳይ ማስረጃ ካልቀረበ፡-

- ☞ የሰው ሀብት ምልመላና መረጣው በብቃት ላይ የተመሠረተ ላይሆን ይችላል።
- ☞ ላልተገባ አሰራር መንገድ ሊከፍት ይችላል።
- ☞ ቅጥሩን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።

4.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

እጩ ተቀጣሪዎች በሰራተኞች የቅጥር ሂደት ላይ እንዲሳተፉ መደረጉ ተገቢነት የሌለው አሰራር ከመሆኑም በተጨማሪ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያወጣውን የቅጥር አፈጻጸም መመሪያ የተከተለ አይደለም። ስለሆነም ኤጀንሲው በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የቅጥር አፈጻጸም መመሪያ መሠረት የሰራተኛ ቅጥር ምልመላና መረጣ የማወዳደሪያ መስፈርት በማዘጋጀት ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር መላክ እና የቅጥር ሂደቱም መመሪያውን ተከትሎ መፈጸም ነበረበት። ከዚህም በተጨማሪ ለተቀጣሪዎች የቀረበው የጽሁፍና የቃል ፈተና ውጤት የሚያሳይ ማስረጃ ካልቀረበ ቅጥሩን ተዓማኒነት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

4.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ለሰራተኞች ቅጥር የቃልና የጽሑፍ ፈተና የተደረገበት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ተገልጾ የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሣቦች ሙሉ በሙሉ ተቀብለናቸዋል። በዚሁ መሰረት የእርምት እርምጃዎች እንደምንወስድ እንገልጻለን።

በአጠቃላይ ኤጀንሲያችን በአለፈው በጀት ዓመት መሥሪያ ቤቱን የማደራጀትና ቁሳቁሶችንና ሰራተኞችን የማሟላት ስራ ላይ የነበረ በመሆኑ የሚከተሉት ሶስት ዋና ዋና ክፍተቶች ነበሩበት።

1. በወቅቱ ብቁ የሰው ኃይል ያልተሟላ የነበረ መሆኑ፣
2. የመንግሥት አዋጆች፣ መመሪያና ደንቦችን ጠንቅቆ ያለማወቅ እና
3. ግዥዎችን በትኩረትና በጥንቃቆ ያለመተግበር ችግሮች፣

እንደነበሩብን ያወቅን ሲሆን፣ እነዚህ ክፍተቶች ቢኖሩም ከተጠያቂነት መራቅ እንደማይቻል የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ባደረገው የ2009 በጀት ዓመት በተገኙ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ማወቅ ችለናል። ያሉብንን ክፍተቶችና ድክመቶች በአግባቡ የተረዳን ስለሆነ በቀጣይ የመንግሥትን የወጪ፣ የንብረት፣ የሰው ኃይልና የተሽከርካሪ አጠቃቀም አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በትክክል ተግባር ላይ ለማዋል ጥረት እንደምናደርግ ለመግለጽ እንወዳለን።

4.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ኤጀንሲው ቅጥሩን ለማከናወን የሚችል የተደራጀ የሰው ኃይል እጥረት ካለበት የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ትብብር በመጠየቅ ቅጥሩ ህጉን ተከትሎ የሚፈጸምበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነበረበት። ከዚህም በተጨማሪ በተቀጠሩ ሠራተኞች የግል ማህደር ውስጥ ከተሰጠው የጽሁፍ ፈተና ውጪ የቃልም ሆነ የጹሁፍ ፈተና ውጤት ያልተያያዘ ወይም ያልቀረበ በመሆኑ ሠራተኞቹ በመመሪያው መሠረት አጥጋቢ ነጥብ አግኝተው መቀጠራቸውን ወይም ተገቢ የሆነ ውድድር

መኖሩን ማረጋገጥ አልተቻለም። በመሆኑም ኤጀንሲው አሰራሩን እንዲያስተካክል እናሳስባለን።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በኤጀንሲው ኃላፊዎችና ሰራተኞች ስለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን።

አባሪ. 1

የቤት ኪራይ የጨረታ ግዥ ቴክኒካል ግምገማ በአግባቡ ባለመከናወኑ ምክንያት አለአግባብ ከመንግሥት ካዝና ወጪ የተደረገ ገንዘብ ዝርዝር ፤

ቀን	የሂሳብ መደብ	የወጪ ቫውቸር ቁጥር	የወጪው ምክንያት	ወጪውን ያዘዘው ኃላፊ	ግዥ የተፈፀመበት ድርጅት	የገንዘቡ ልክ
26/03/09	6257	0873242	የተለያዩ የኤሌክትሪክ እቃዎች ግዥ	አቶ በቀለ ንጉሤ	ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን	5,000.00
08/05/09	6257	198642	የኤሌክትሪክ ኃይል ለመጨመር ክፍያ	አቶ በቀለ ንጉሤ	ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን	610,221.29
29/09/09	6251	185043	የኔትዎርክ ማስፋፊያ	አቶ በቀለ ንጉሤ	ለአቶ ሰለሞን ሹፈር	138,000.00
ድምር						**753,221.29**

አባሪ. 2

ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ በውስን ጨረታ የተፈጸመ የፈርኒቸር እቃዎች ግዥ፤

ቀን	የወጪ ቫውቸር ቁጥር	ገንዘቡ የተከፈለው	የሂሳብ መደብ	የገንዘቡ ልክ
06/03/09	0873202	ምንአየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባኒያ	4211	374,522.51
27/03/09	0873247	ሜይስዊ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር	6314	460,436.44
05/05/09	0873289	ምንአየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባኒያ	6314	1,485,775.77
ድምር				**2,320,734.72**

<u>በጨረታ መገዛት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ፤</u>

ቀን	የጆርናል ቫውቸር ቁጥር		ገንዘቡ የተከፈለው	የዕቃው አይነት	የሂሳብ መደብ	የገንዘቡ ልክ
19/03/09	JV	198609	ምንአየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባኒያ	የፈርኒቸር እቃዎች	6314	117,090.01
19/03/09	JV	198609	ምንአየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባኒያ	የፈርኒቸር እቃዎች	6314	51,849.99
19/03/09	JV	198609	ምንአየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባኒያ	የፈርኒቸር እቃዎች	6314	73,034.05
12/10/09	PV	185067	ሜይስዊ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	የመጸሀፍ መደርደርያ ሼልፍ	4211	153,000.00
16/10/09	JV	198698	ምንአየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባኒያ	የተለያዩ ወንበሮች	6314	106,099.87
ድምር						503,073.92

አባሪ. 4

<u>የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	ቀን	የወጪ ቫውቸር ቁጥር	የወጭው ምክንያት	የተከፈለዉ ድርጅት (ግለሰብ)ስም	የሂሳብ መደብ ቁጥር	የገንዘብ መጠን
1	28/02/09	JV-198614	ለሞዛይክ እና አኮሬም ላይት	ዋው ፕሪም ሀውስ ኃ/የተ/የግ/ማህ	6313	26,917.51
2	28/02/09	JV-198614	ለአበቦች ግዥ	ኃይሉ እና ጓደኞቹ አበባ መሸጫ	6219	17,799.00
3	28/03/09	JV-198625	ለአበቦች ግዥ	ሀይቱ ተባረክ እና ጓደኞቹ ማ/መ/ስ/ህ/ሽ/ማ	6219	19,737.00
4	28/03/09	JV198624	ማከፋፈያ	አይቲ ቪሌጅ	6313	4,700.00
5	27/04/09	JV 198638	ለተለያዩ አበቦች	ኤል.አስ.ኤች ሆም ኤንድ ቢዮንድ ትሬድ	6212	4,925.06
6	27/04/09	JV 198638	ቲቪ ስታንድ	ማትዮስ ትሬዲንግ	6314	9,500.00
7	27/04/09	JV198638	የቡና ጠረጴዛ	ሰርካለም ፈጄ የቤትና የቢሮ መስዋቢያዎች	6314	10,397.12
8	27/04/09	JV198638	ግለስ ቦዊል	ሸዋ ሾፒንግ ሴንተር	6219	6,124.64
ድምር						**100,100.33**

አባሪ. 5

ከ10% በላይ ያልተሰራበት የመደበኛ በጀት ዝርዝር፤

የወጪ ሒሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ በጀት	ያልተሰራበት በጀት	
			የገንዘቡ ልክ	በፐርሰንት (%)
የበጀት ኮድ 279/01/01				
6211	87,000.00	24,043.51	62,956.49	72
6212	2,604,794.00	1,351,335.09	1,253,458.91	48
6231	500,000.00	197,875.89	302,124.11	60
6232	200,000.00	150,429.00	49,571.00	25
6244	100,000.00	58,126.74	41,873.26	42
6253	300,000.00	35,119.20	264,880.80	88
6256	56,000.00	44,498.09	11,501.91	21
6258	350,000.00	311,379.83	38,620.17	11
6259	60,000.00	3,159.48	56,840.52	95
6271	115,000.00	87,329.67	27,670.33	24
6314	5,000,000.00	4,128,604.54	871,395.46	17
ድምር			**2,980,892.96**	

አባሪ. 6

ስለተራፊው በጀት የተሰጠ ዝርዝር መግለጫ፤

የሂሳብ መደብ ቁጥር	በጀቱ ሊተርፍ የቻለበት ምክንያት
6211	ኤጀንሲው አዲስ በመሆኑ ምክንያት የግማሽ ዓመት ግዥ ብቻ በመፈጸሙ ነው፡፡
6212	የተገዛው አላቂ እቃ በቂ በመሆኑ ነው፡፡
6231	የአበል ክፍያ ባለመቅረቡ ምክንያት ነው፡፡
6232	የትራንስፖርት ክፍያ ባለመቅረቡ ምክንያት ነው፡፡
6244	በወቅቱ ሥራዎች ባለመተግበራቸው ምክንያት ነው፡፡
6253	አግልግሎቱ ባለማቅረቡ ምክንያት ክፍያ በመዘግየቱ ነው፡፡
6256	የአገልግሎት ክፍያ ባለመኖሩ ነው፡፡
6258	የግንቦትና የሰኔ 2009 ዓ.ም ክፍያዎች ዘግይተው በመምጣታቸው ነው፡ ፡
6259	የግንቦትና የሰኔ 2009 ዓ.ም ክፍያዎች ዘግይተው በመምጣታቸው ነው፡ ፡
6271	በበጀት ዓመቱ የሥልጠና ፍላጎት ስላልታቀደ ነው፡፡
6314	አቅራቢው ድርጅት የክፍያ ጥያቄ ባለማቅረባቸው ነው፡፡

አባሪ. 7

<u>የሰራተኞች ቅጥር የቃል እና የጽሑፍ ፈተና</u>

<u>የተደረገበት ማስረጃ ያልቀረበለት ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	የሰራተኛ ስም	የተቀጠሩበት የሥራ መደብ	የተቀጠሩበት ቀን
1.	እጅጋየሁ የሱፍ	የንብረት ጸሐፊ	መስከረም 1/2009
2.	ሚካኤል ተስፋዬ	ጀማሪ ኢንፍራስትራክቸር	መስከረም 1/2009
3.	እግዚእ ፍቃዱ	ጀማሪ ኢንፍራስትራክቸር	መስከረም 1/2009
4.	በርናባስ ገ/ሊባኖስ	ጀማሪ ኢንፍራስትራክቸር	መስከረም 1/2009
5.	ፍላጎት አርጋው	ጀማሪ ኢንፍራስትራክቸር	መስከረም 1/2009
6.	ጎይቶም አርአያ	ጀማሪ ኢንፍራስትራክቸር	መስከረም 1/2009
7.	ጀማል አብደላ	የህግ ዳይሬክተር	መስከረም 10/2009
8.	አለምነሽ ሙላቱ	የህግ ባለሙያ III	መስከረም 14/2009
9.	አማረች ገ/ኢየሱስ	ጀማሪ ኢንፍራስትራክቸር	ጥቅምት 1/2009
10.	ቢኒያም መሀመድ	እክስፔዳይተር	ጥቅምት 1/2009
11.	አለማየሁ ተገኔ	ሹፌር II	ጥቅምት 1/2009
12.	ኤርምያስ አጥናፉ	ሹፌር I	ጥቅምት 1/2009
13.	እሌኒ ደባሽ	ጀማሪ የበጀት ባለሙያ	ጥቅምት 10/2009
14.	ምህረት ለገሰ	መልክተኛ	ጥቅምት 15/2009
15.	አክሊል ርእስ	የሴቶች ወጣቶች ጉዳይ ባለሙያ	ጥቅምት 15/2009
16.	ተስፋ ደሴው	ሹፌር I	ህዳር 7/2009
17.	ምስራቅ ዘገየ	ከፍተኛ የበጀት ባለሙያ	ጥር 24/2009
18.	ታምራት ነገሰ	ጀማሪ ኦዲት ባለሙያ	ሰኔ 14/2009

በሥራ አመራር ሪፖርት በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር

የኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት ስም:- ____________________________

ኦዲት የተደረገው ሂሳብ በጀት ዓመት:- ____________________________

የተዘጋጀበት ቀን፡ - ___________________

ተራ ቁጥር	የኦዲት ግኝቶች	የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች	እስከአሁን የተወሰዱ ማስተካከያ እርምጃዎች	ቀሪ ማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ የሚደረጉበት ጊዜ	ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል	ምርመራ

ማሳሰቢያ:- ይህ መርዓ-ግብር እና የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤትዎ እንደደረሰ የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ ተሞልቶ በ7 ቀናት ውስጥ ለመ/ቤታችን ካልተመለሰ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በምናቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ "ለኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር መልስ ያልላኩ መሥሪያ ቤቶች" ዝርዝር ውስጥ እና እርምጃ አለመወሰዱ ተጠቅሶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን እንገልፃለን።